# *በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የማታ ሦስተኛ አመት መማሪያ ክፍል ‹‹02›› አስር ሴቶች እና አራት ወንድ የአማርኛ ቋንቋ ሰልጣኝ ተማሪዎችን አንቀጽን የመጻፍ ችግር እንዴት መቅረፍ እችላለሁ?*

*መብራት በሪሁን[3] የአማርኛ ቋንቋ ሌክቸረር፣ በቋንቋ ትምህርት ክፍል፣ እንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ እንጅባራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኢሜል mebratuberihun21@gmail.com*

**አጠቃሎ/Abstract**

*የዚህ ድርጊታዊ ምርምር ዋነኛ አላማ በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የማታ ሦስተኛ አመት መማሪያ ክፍል ‹‹02›› አስር ሴቶች እና አራት ወንድ የአማርኛ ቋንቋ ሰልጣኝ ተማሪዎችን አንቀጽን የመጻፍ ችግር መቅረፍ ነው። የጥናቱ ዝርዝር አላማዎችም1.የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶችን መለየት። 2.የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነትና አመለከካትን መረዳት። 3.የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽ የመጻፍ ችግርን መቅረፍ ናቸው። የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎ ደግሞ 1.የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን መፃፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? 2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን ለመፃፍ ያላቸው ተነሳሽነትና አመለከካት ምን ይመስላል? 3. የጥናቱ ተሳታፊዎችን አንቀጽን የመጻፍ ችግር ለመቅረፍ የሚረዱ ስትራቴጂዎች ምን ምን ናቸው? የዚህ ጥናት ንድፍ ገላጭ ሲሆን፣ ዘዴው ደግሞ አይነታዊ እና መጠናዊ ነው። የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ እና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው። በጽሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት አንቀጽን ለመጻፍ ዝቅተኛ መሆን ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡መምህራን ሲያስተምሩ ለአንቀጽ ትኩረት ሰጥተው አለማስተማር፤የጽህፈት ክሂልን ለመለማመድ የሚሰጠው ጊዜ በቂ ስለማይሆን፤መምህራን የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ ቶሎ ግብረ መልስ ስለማይሰጡ፤ የተማሪዎች ለጽህፈት ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን፤ መምህራን ተማሪዎችን ከማበረታታት ይልቅ ማሸማቀቅ፤በተግባር ለመለማመድ ሰፊ ዕድል አለማግኘት፣ በተግባር እየፃፉ ከማለማመድ ይልቅ በማውራት /በገለፃ/ ማለፍ የሚሉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አስተያየት ሁሉም የሚመለከታቸው የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም የትምህርት አመራሮችና መምህራን ዕለት ተዕለት በመማር ማስተማር ተግባር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየትና በማቀድ ድርጊታዊ ጥናትና ምርምር በማድረግ በከፊልም ቢሆን ችግሮችን መቅረፍ ስለሚቻል መስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አንቀጽ መጻፍን የተለያዩ ተግባራትን በማዘጋጀትና ግብረ መልስ በመስጠት በተግባር ማለማመድ ቢቻል የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ ለጽህፍት መሰረቱ ፊደል በመሆኑ የፊደል ቅርፆችን ትኩረት ሰጥቶ ለመለየት የፊደል ገበታው መለየት የለበትም፡፡ ተማሪዎችን ከግል ተግባራቸው በተጨማሪ በቡድንና በጥንድ በጋራ ተወያይተው የሚጽፉትን የጋራ ተግባር ብንሰጥ የበለጠ መማማር ይችላሉ፡፡አንቀጽን መጻፍ የተግባር ልምምድን የሚፈልግ መልዕክት/ሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን ከምርምሩ መረዳት ተችሏል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች 98% ያክሉን ችግር ቀርፈዋል፤ ቢባልም 2% ያክሉ ችግር ያልተቀረፈ መሆኑን ከተገለፀው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ከሥነ ፍጥረታት ሁሉ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ የእርስ በርስ መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የቋንቋ ምንነትን ትምህርት ሚኒስቴር ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ (2004፣ 2) ላይ "ቋንቋ ከሰዎች አንደበት የሚፈልቅ ድምፃዊ መግባቢያ ነው፡፡ ሰዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሐሳባቸውን ለሌሎች ሰዎች ያጋራሉ፡፡ የሌሎችንም ሐሳብ እንዲሁ በቋንቋ አማካይነት ይቀበላሉ" በማለት ገልፆታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ Jordan (1980፣ 38) የቋንቋን ምንነት ሲገልጹ ‹‹ቋንቋ ከአንደበት ክፍሎች በሚፈልቁ የንግግር ድምፆች አማካይነት ሰዎች እርስ በርሳቸው ለተግባቦት ተግባር የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው›› ሲሉ ገልጸውታል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ማለት ደግሞ በቋንቋው በሰለጠነ ባለሙያ የመማር ማስተማርን ሂደት የሚያግዙ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተውለት በተወሰነ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሰጥ አጠቃላይ የቋንቋ ሥርዓትና አጠቃቀምን የሚመለከት ስልጠና ነው፡፡ Lewis and Hill (1985፣ 22) የቋንቋ ትምህርትን ምንነት ‹‹የቋንቋ ትምህርት ማለት ቋንቋን ማስተማር እንዲሁም መማር ማለት ነው›› በማለት ገልጸውታል፡፡

እንዲሁም ባየ (2000፣ xxv) የቋንቋ ትምህርት ምንነትን ‹‹ራሱን የቻለ መርህ ግብር ሆኖ በራሱ ዘዴና አላማ መሰረት በወጉ በሰለጠኑ መምህራን አማካይነት ትምህርቱን ማስተማር ማለት ነው፡፡ አንድ ተማሪ ቋንቋን ተማረ የሚባለው የቋንቋን ክሂሎች ከነስርዓቱ ተገንዝቦ በተገቢ ሁኔታ መገልገል ሲችል ነው›› በማለት ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ ቋንቋን መማር ማለት የቋንቋውን ሰዋስው ማወቅ ብቻ ሳይሆን አገባቡን ከነአገልግሎቱ በማወቅ የመገልገል ብቃት ማሳደግም ጭምር ነው፡፡ በአጠቃላይ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ በልዩ ልዩ የመስተጋብር አውዶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በመሳተፍ ብቃት ያለውን ተራክቦ የመፍጠር ችሎታን ያካትታል፡፡ ቋንቋን በአግባቡ ለመጠቀም ቋንቋውንና የአጠቃቀም ሥርዓቱን በተገቢ ሁኔታ መማር አስፈላጊ መሆኑን Harmar (1991) እና Stern (1983) አጽንኦት በመስጠት ገልጸዋል፡፡

ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ በዋናነት የሚነሰው ጉዳይ ማንን? ምንን? እንዴት? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን አጠቃላይ ዳራ፣ የትምህርቱን ይዘት መምረጥና የማስተማሪያ ስልቶችን መወሰንን የሚያመላክት ነው፡፡ በቅድሚያ ይዘትን ለመምረጥና ስልቶችን ለመወሰን የተማሪዎችን ዳራ በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

#### 1.1.1 የአንቀጽ ምንነት

አንቀጽ ማለት የአረፍተ ነገሮች ስብስብ ሲሆን፣ ስለአንድ ሃሳብ ብቻ የሚያወራ፣ የሚተርክ፣ የሚያትት አነስተኛ የድርሰት አካል ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አንድ የተሟላ ድርሰት የሚባለው የአንቀፆች ስብስብ ነው፡፡ የድርሰትን አላማ ከግብ ለማድረስ ልዩ ልዩ ሃሳቦች በአንቀጽ በአንቀጽ ተከፋፍለው ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ሃሳቦች ራሳቸውን የቻሉ የድርሰት ክፍል ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት

እንደሚቻለው አንቀጽ በድርሰት ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ሃሳቦች ለየብቻ ተለየተው የሚገለጽበት የድርሰት አካል ነው፡፡ ምንጊዜም በአንድ አንቀጽ ውስጥ ሊኖር የሚችለው አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ ነው፡፡

### 1.1.2 **የአንቀፅ ባህሪያት**

አንድ አንቀጽ ሊያሟላቸው የሚገቡ መስረታዊ ነገሮች ወይም ባህሪያት **አንድነት**፣ **ግጥምጥምነት** እና **አፅንኦት** ናቸው፡፡ የአንቀጽ መልዕክት አስተላላፊነት የሚጕላው እነዚህ ባህሪያት ሲሟሉ ነው፡፡

### 1.1.3 **የአንቀፅ ጠቀሜታ**

ፀሐፊ ወይም ደራሲ ድርሰቱን በአንቀጽ ከፋፍሎ የሚጽፈው በምክንያት ነው፡፡ ድርሰት በአንቀጽ እየተከፋፈለ የሚቀርብበት ዋናው ምክንያት በድርሰቱ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ሃሳብ ከፋፍሎ ለማቅረብ የሚረዳ ቅርፅ ስለሆነ ነው፡፡ ቅርጹና ሥርዓቱ አንድን ነጠላ ሃሳብ ብቻ ለማቅረብ የሚፈቅድ በመሆኑ አንባቢያንን(ተደራሲያንን) እና ደራሲን ለመርዳት ሲባል አንድን ድርሰት በአንቀጾች ከፋፍሎ ማቅረብን ምክንያታዊ ያደርገዋል ማለት ነው፡፡

### 1.1.4 **በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ የአረፍተ ነገር አይነቶች**

በአንድ አንቀጽ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ የአረፍተ ነገር አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ኃይለ ቃል እና ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ይባላሉ፡፡

በአንቀጽ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ አረፍተ ነገሮችን ብዛት የሚወስኑ ሁለት አበይት ምክንያቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ኃይል ቃሉ /አንቀጹ/ የያዘው ሃሳብ ስፋትና ጥበት እንዲሁም የደራሲው አላማ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በአንቀጹ የሚገኙ ዝርዝር አረፍተ ነገሮች ብዙ ወይም ጥቂት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 1.2. **የጥናቱ ችግር ማብራሪያ**

እነዚህ የጥናቱ ተተኳሪ ሰልጣኞችን ከአንደኛ አመት ጀምሮ የተለያዩ ኮርሶችን ሳስተምር የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ እንዲሁም የፕሮጀክት ስራቸውን ሲሰሩ በማርምበት ጊዜ የሚጽፉት አንቀጽ የአንቀጽን መስፈርት ያማያሟላ፤ ሙሉ ሀሳብ የማያስተላልፍ፤ በአንድ አንቀጽ ውስጥ በርካታ ሀሳቦች የተካተቱበት፤ አስፈላጊ ስርዓተ ነጥቦች ያልገቡበት፣ የአንቀጹ አንድነትና ግጥምጥምነት የጎደሉበት፤ አረፍተነገሮቹ ትክክለኛውን አወቃቀር ያልተከተሉ እየሆነ የሚጽፉት አንቀጽ ችግሮች ነበሩበት፡፡ በመሆኑም በመደበኛው መማር ማስተማር ችግሩ ጎልቶ የሚታይባቸውን ሰልጣኞች፡-

- ችግራቸውን በዝርዝር ነቅሶ በማውጣት እንዲያስተካክሉ አደርግ ነበር፡፡
- በርካታ የሚጽፏቸውን ተግባራት በተደጋጋሚ እሰጣቸው ነበር፤ ነገር ግን አብዛኞቹ ሰልጣኞች ሳይሰሩ ይመጡና የተለያዩ ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡
- እንዲጽፉ ሲታዘዙ ውጤት የሌለው ከሆነ ለመስራት አይነሳሱም፤ አይፈልጉም ነበር፡፡
- የተሰጣቸውን የቤት ስራ ራሳቸው ከመሞከር ይልቅ ለሰው አሰርተው ይመጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ አንቀጽን መጻፍ ላይ እንዳይሻሻሉ ያደርጋቸዋል፡፡
- በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ አድርግ ነበር፡፡ ነገር ግን ጊዜው በቂ አይደለም፡፡

- አንቀጽ መጻፍን ለማለማመድ ቲቶርያል እጠራቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ በትርፍ ጊዜያቸው ሰርተው ስለሚማሩ ቲቶርያል ላይ አይገኙም፡፡ ይህ ደግሞ አንዱ እንቅፋት ነበር፡፡

- በመደበኛው መማር ማስተማር ችግራቸውን ለመፍታት ብዙ ጥረት አድርጌለሁ፡፡ ነገር ግን ችግሩ ሳይቀረፍ እስከ ሦስተኛ አመት ዘለቀ፡፡

- በሦስተኛው አመት አንደኛ ወሰነ ትምህርት **የዘገባ አፃፃፍ** /**Report Writing** (MT 321) ኮርስ በማስተምርበት ጊዜ በተለይም የ14 ሰልጣኞች አንቀጽን መጻፍ ችግር ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ በድርጊታዊ ምርምር መፈታት እንዳለበት በመወሰን ወደ ጥናት ገባሁ፡፡

   - **ችግሩ ባይቀረፍ የሚያስከትለው ጉዳት**

- ተጠኚዎቹ ሰልጣኞች በእውቀትም ሆነ በውጤት ተጎጂ ይሆናሉ፡፡
- ሰልጣኞቹ ከነችግሩ ቢመረቁና ቢወጡ ነገ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ይጎዳሉ፡፡
- ከሚያስተምሯቸው ተማሪዎች አልፎ ማህበረሰብንና አገርን ይጎዳል፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን መፃፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን ለመፃፍ ያላቸው ተነሳሽነትና አመለከካት ምን ይመስላል?
3. የጥናቱ ተሳታፊዎችን አንቀጽን የመጻፍ ችግር ለመቅረፍ የሚረዱ ስትራቴጂዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ አጠቃላይ አላማ

የዚህ ድርጊታዊ ምርምር ዋና አላማ በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የማታ ሦስተኛ አመት መማሪያ ክፍል ‹‹02›› አስር ሴቶች እና አራት ወንድ የአማርኛ ሰልጣኝ ተማሪዎችን አንቀጽን የመጻፍ ችግር መቅረፍ ነው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዝርዝር አላማ

1. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶችን መለየት፡፡
2. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነትና አመለከካትን መረዳት፡፡
3. የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽ የመጻፍ ችግርን መቅረፍ ናቸው፡፡

## 1.6 የጥናቱ አስፈላጊነት

ማንኛውም ጥናትና ምርምር ሲካሄድ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ይህ ድርጊታዊ ምርምርም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. በዚህ ድርጊታዊ ጥናትና ምርምር የሚሳተፉ ሰልጣኞች/ተማሪዎች አንቀጽን መጻፍ ችግርን ስለሚቀርፉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡
2. አጥኚውን ደግሞ በቀጣይ በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንዳለበት መሰረት ሆኖ ይጠቅመዋል፡፡
3. ለማህበረሰቡም አንቀጽን ለመጻፍ የተሻሉ መምህራንን በማብቃት ተተኪ ትውልድን በመቅረፅ ረገድ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡
4. እንዲሁም በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚደረጉ ቀጣይ ጥናቶች እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

የዚህ ጥናት ንድፍ ገላጭ ሲሆን፣ ዘዴው ደግሞ አይነታዊ እና መጠናዊ ነው፡፡ ስለዚህ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተመራማሪው የሚያጠናቸውን ጉዳዮች መረጃዎችን ተንትኖ በትረካዊ ወይም ገለጻዊ መንገድ የሚያቀርብበት ዘዴ ሲሆን በመጠናዊ ዘዴ ደግሞ በቁጥር የሚገልጽበት ነው፡፡

**2.1. የጥናቱ አካባይ**

በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በ2014 ዓ.ም መማሪያ ክፍል ‹‹02›› የሚማሩ የማታ አማርኛ ቋንቋ 3ኛ አመት ሰልጣኞች ሲሆኑ፣ ብዛታቸው ወንድ 12 (አስራ ሁለት) ሴት 33 (ሰላሳ ሶስት) በጠቅላላው 45 (አርባ አምስት) ሰልጣኞች ናቸው፡፡

**2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች**

በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በ2014 ዓ.ም መማሪያ ክፍል ‹‹02›› የሚማሩ የማታ አማርኛ ቋንቋ 3ኛ አመት ሰልጣኞች መካከል አንቀጽን የመጻፍ ችግር የሚታይባቸው 4(አራት) ወንዶች እና 10(አስር) ሴቶች በጠቅላላው 14(አስራ አራት) ሰልጣኞች በቀጥታ የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

**2.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ**

በእንጅባራ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ቋንቋ ትምህርት ክፍል በ2014 ዓ.ም መማሪያ ክፍል ‹‹02›› የሚማሩ የማታ አማርኛ ቋንቋ 3ኛ አመት 45(አርባ አምስት) ሰልጣኞች መካከል አንቀጽን የመጻፍ ችግር የሚታይባቸው 4(አራት) ወንዶች እና 10(አስር) ሴቶች በጠቅላላው 14 (አስራ አራት) ሰልጣኞች በአላማ ተኮር (purposive sampling) ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

**2.4. የመረጃ ምንጮች**

ዋና የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገለው በቀጥታ ከተተኳሪ ተሳታፊዎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰበ መረጃ ነው፡፡

**2.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች**

2.5.1 ምልከታ

2.5.2 የጽሑፍ መጠይቅ

**2.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ**

የዚህ ጥናት መረጃ ከጥናቱ ተተኳሪዎች በቀጥታ በምልከታ እና በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰበ ሲሆን፣ የተሰበሰቡ መረጃዎችም በአይነታዊ የምርምር ዘዴ በገላጭ ስልት በመተንተን የጥናቱ ውጤትም ተብራርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃው በመቶኛ ስሌትም (በፐርሰንት) የተገለጸበት አግባብ አለ፡፡

**2.7 መረጃን መተንተንና መተርጎም**

**2.7.1 ቅድመ ትግበራ መረጃ ትንተና**

ከጥናቱ ተተኳሪ ሰልጣኞች በምልከታ እና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በዋናነት በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ተብራርቶና በመቶኛ ተገልፆ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡- በተጠኚዎች በዝግ መጠይቆች የተሰጡ መረጃዎች አማራጮች፡- 5= በጣም እስማማለሁ 4= እስማማለሁ 3= መወሰን አልችልም 2= አልስማማም 1= በጣም አልስማማም

ሠንጠረዥ 1. ቅድመ ትግበራ መረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ የሆነው መምህራን ሲያስተምሩ ትኩረት አለመስጠት ነው፡፡ | 8 (57%) | 2 (14%) | --- | 3 (22%) | 1 (7%) |
| 2 | አንቀጽ መጻፍን ለመለማመድ የሚሰጠው ጊዜ በቂ ስለማይሆን ነው፡፡ | 7 (50%) | 4 (29%) | --- | 3 (22%) | --- |
| 3 | 1ኛ ደረጃ እና 2ኛ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለአንቀጽ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡ | 1 (7%) | 2 (14%) | 4 (29%) | 3 (22%) | 4 (29%) |
| 4 | መምህራን አንቀጽ መጻፍን ሲያስተምሩ ቶሎ ግብረ መልስ የመስጠት ችግር አለ፡፡ | 6 (43%) | 6 (43%) | 1 (7%) | 1 (7%) | --- |
| 5 | ተማሪዎች አንቀጽን መጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ዝቅተኛ ነው፡፡ | 3 (22%) | 7 (50%) | 2 (14%) | 1 (7%) | 1 (7%) |
| 6 | አንቀጽን መጻፍ አስቸጋሪ እና ውስብስብ ነው፡፡ | 2 (14%) | 1 (7%) | 3 (22%) | 6 (43%) | 2 (14%) |

ከላይ ከሠንጠረዥ 1 ላይ እንደተቀመጠው *አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ መሆን መምህራን ሲያስተምሩ ትኩረት አለመስጠት ነው፤* ለሚለው መጠይቅ በጣም እስማማለሁ 8(57%)፣ እስማማለሁ 2(14%)፣ አልስማማም 3(22%)፣ በጣም አልስማማም 1(7%) በማለት ተተኳሪ ሰልጣኞች መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው ከተጠኚዎች የተገኘው መረጃ አብዛኛው ማለትም 10(71%) የሰጡት ሀሳብ መምህራን ሲያስተምሩ ትኩረት ስለማይሰጡ አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል የሚለውን ነው፡፡

*አንቀጽ መጻፍን ለመለማመድ የሚሰጠው ጊዜ በቂ ስለማይሆን ነው፤* ለሚለው መጠይቅ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 7(50%)፣ እስማማለሁ 4(29%)፣ አልስማማም 3(22%) በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም 11(79%) መረጃ ሰጪዎች ወይም ተጠኚዎች እንደገለፁት አንቀጽን ለመጻፍ በቂ ጊዜ ተመድቦለት የተግባር ልምምድ የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ መሆን አንዱ ምክንያት የሚሰጠው ጊዜ አነስተኛ መሆን ነው፡፡

*አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለአንቀጽ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፤* ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅም በጣም እስማማለሁ 1(7%)፣ እስማማለሁ 2(14%)፣ መወሰን አልችልም 4(29%)፣ አልስማማም 3(22%)፣ በጣም አልስማማም 4(29%) ብለው ተጠኚዎቹ መልሰዋል፡፡ ከዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው ደግሞ ከ14 ተጠኚዎች መካከል መወሰን አልችልም 4(29%)፣ አልስማማም እና በጣም አልስማማም 7(50%) በማለት ምላሽ የሰጡ በመሆናቸው 1ኛ ደረጃና 2ኛ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለአንቀጽ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

እንዲሁም *መምህራን አንቀጽ መጻፍን ሲያስተምሩ ቶሎ ግብረ መልስ የመስጠት ችግር አለባቸው* ተብለው ሲጠየቁ፤ በጣም እስማማለሁ 6(43%)፣ እስማማለሁ 6(43%)፣ መወሰን አልችልም 1(7%)፣ አልስማማም 1(7%)፣ ብለው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አንቀጽ መጻፍን በተግባር ልምምድ ጊዜ መምህራን ሳይውል ሳያድር ቶሎ ግብረ መልስ የማይሰጡ መሆናቸውን 12(86%)

ተጠኚዎች በመረጃቸው አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ለአንቀጽ ጽሕፈት ዝቅተኛ መሆን አንዱ ምክንያት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

*ተማሪዎች ለጽህፈት ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ዝቅተኛ ነው፤* ለሚለው ሀሳብም በጣም እስማማለሁ 3(22%)፣ እስማማለሁ 7(50%)፣ መወሰን አልችልም 2(14%)፣ አልስማማም 1(7%)፣ በጣም አልስማማም1(7%) የሚለውን መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ላይም መረዳት የሚቻለው 10(72%) ተጠኚዎች ከሰጡት መረጃ በመነሳት ለአንቀጽ ጽሕፈት ዝቅተኛ መሆን የተማሪዎች አንቀጽን ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት አነስተኛ መሆን ሌላው ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

በመጨረሻም *አንቀጽን መጻፍ አስቸጋሪ እና ውስብስብ ነው፤* ተብለው ለተጠየቁት መጠይቅ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 2(14%)፣ እስማማለሁ 1(7%)፣ መወሰን አልችልም 3(22%)፣ አልስማማም 6(43%)፣ በጣም አልስማማም 2(14%) በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህ መረጃ የሚያስረዳን ደግሞ 8(57%) ተጠኚዎች አልስማማም እና በጣም አልስማማም ብለው ምላሽ የሰጡ በመሆናቸው አንቀጽን መጻፍ በተለየ መልኩ ከባድና አስቸጋሪ አለመሆኑን ማሳያ ነው፡፡

በተጠኚዎች በክፍት ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. *ለአንቀጽ ጽሕፈት ዝቅተኛ መሆን ሌሎች ምክንያቶች ካሉ ብትገልጹ?* ተብለው ሲጠየቁ በተግባር ለመለማመድ ሰፊ ዕድል አለማግኘት፣ በተግባር እየፃፉ ከመለማመድ ይልቅ በማውራት ማለፍ፣ መምህራን የተግባር ልምምድ ሰጥተው ማስተካካያ እርማት አለመስጠት፣ መምህራን ትኩረት ሰጥተው አለማስተማር፣ ተማሪዎቹ በግላቸው ጥረት አለማድረግ የሚሉ ተጨማሪ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡

2. *አንቀጽን መጻፍ ትምህርት መነሳሳት እና ፍላጎት እንዳይኖር የሚያደርጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?* ለሚለው መጠይቅ ደግሞ ከማበረታታት ይልቅ ማሸማቀቅና መዝለፍ፣ ለጽህፈት ክሂል ያለው አመለካከትና ግንዛቤ ትክክለኛ አለመሆን፣ ግዴሌሽነት፣ አልችልም ብሎ ተስፋ መቁረጥ፣ የመሳሰሉት ጉዳዮች መነሳሳቱና ፍላጎት እንዲቀንስ ያደርጋሉ ብለዋል፡፡

3. *የአንቀጽ መጻፍ ዝቅተኛነት ችግርን እንዴት መቅረፍ ይቻላል?* ለሚለው መጠይቅም ለልምምድ ሰፊ ጊዜ መስጠት፣ በየጊዜው የተግባር ልምምድ ማድረግ፣ ማበረታታት፣ ድጋፍና ግብረመልስ መስጠት፣ በቡድንና በጥንድ በጋራ በመወያየትና በመረዳዳት መፃፍ፣ በተግባር የሚሰሩ የክፍልና የቤት ስራዎችን መስጠት ችግሩን ሊፈታው ይችላል የሚል መረጃ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ከምልከታ እና ከጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ በመነሳት እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል።

- የጥናቱ ተሳታፊዎች አንቀጽን መጻፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ለሚለው ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ መምህራን ለአንቀጽ ትኩረት ሰጥተው ያላማስተማር፤ ለተግባር ልምምድ የሚሰጠው ጊዜ በቂ አለመሆን፤ ለተማሪዎች ገንቢና ጠቃሚ ግብረ መልስ ቶሎ ቶሎ አለመስጠት፤ ተማሪዎች አንቀጽን ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት አነስተኛ መሆን፤ እንዲሁም ከምልከታ ከተገኘው መረጃም መታዘብ እንደተቻለው ቸልተኛ መሆንና እንዲጽፉ ሲታዘዙ ታማኒነት የሌላቸው የተለያዩ ምክንያቶችን ማቅረብ ለአንቀጽ ጽሕፈት ዝቅተኛ መሆን በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

- የጥናቱ ተሳታፊዎች ለአንቀጽ ጽሕፈት ያላቸው ተነሳሽነትና አመለከካት ምን ይመስላል? ለሚለው ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ተነሳሽነቱና ፍላጎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን በምልከታና

ከመረጃው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የተጠቀሰው መምህራን የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ ማበረታታትና መደገፍ ሲገባቸው ማሸማቀቅ፣ መዝለፍ፣ ተስፋ ማስቆረጥ፣ የመሳሰሉት ጉዳዮች ለተነሳሽነት እንቅፋት መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡

- የጥናቱ ተሳታፊዎችን ዝቅተኛ የመፃፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል የሚረዱ ስትራቴጂዎች ምን ምን ናቸው? ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ደግሞ ክፍት መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ላይ እንደተሰጠው ሰፊ የልምምድ ጊዜ በመስጠት፣ በየጊዜው ተግባራትን መስጠት፣ በግል የሚሰሩ፣ በጥንድ እና በቡድን በመወያየት የሚሰሩ ተግባራትን መስጠት፣ ከመምህራን ማበረታቻ፣ ድጋፍና ግብረመልስ እየወሰዱ መለማመድ ዝቅተኛ የአንቀጽ ጽሕፈት ችግርን ለማሻሻል የሚጠቅም መሆኑን ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

### 2.7.2 ዋና ዋና የጥናቱ ግኝቶች

በጽሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት አንቀጽን ለመጻፍ ዝቅተኛ መሆን ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- መምህራን ሲያስተምሩ ለአንቀጽ ትኩረት ሰጥተው አለማስተማር፤
- የጽህፈት ክሂልን ለመለማመድ የሚሰጠው ጊዜ በቂ ስለማይሆን፤
- መምህራን የጽህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ ቶሎ ግብረ መልስ ስለማይሰጡ፤
- የተማሪዎች ለጽህፈት ክሂል ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን፤
- መምህራን ተማሪዎችን ከማበረታታት ይልቅ ማሸማቀቅ፤
- በተግባር ለመለማመድ ሰፊ ዕድል አለማግኘት፣ በተግባር እየፃፉ ከማለማመድ ይልቅ በማውራት /በገለፃ/ ማለፍ የሚሉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 2.8. የድርጊት መርሀ ግብር

### 2.8.1 ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ ስልቶች

- የዘመድ/የግል ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡
- የመስርያ ቤት ደብዳቤ በቡድን እንዲጽፉ ማድረግ፡፡
- ራሳቸው በመረጡት ርዕስ አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡
- ርዕስ በመስጠት አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡

### 2.8.2. የተጠቆሙ ስልቶች ወደ ተግባር የሚለወጡበት ዘዴ

ሠንጠረዥ 2. የተጠቆሙ ስልቶች ወደ ተግባር የሚለወጡበት ዘዴ

| ተ.ቁ | ተግባራት | ጊዜ | የሚወስደው የጊዜ መጠን | | ተሳታፊዎች | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የዘመድ/የግል ደብዳቤ በግላቸው እንዲጽፉ ማድረግ | መጋቢት | ሁለት ሳምንት | 2 ዙር | እኔና ተማሪዎች | |
| 2 | የመስርያ ቤት ደብዳቤ በቡድን እንዲጽፉ ማድረግ | ሚያዚያ | ሁለት ሳምንት | 2 ዙር | እኔና ተማሪዎች | |
| 3 | ራሳቸው በመረጡት ርዕስ በጥንድ አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ | ሚያዚያ | አንድ ሳምንት | 2 ዙር | እኔና ተማሪዎች | |
| 4 | ርዕስ በመስጠት አንቀጽ በግላቸው እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ | ግንቦት | አንድ ሳምንት | 2 ዙር | እኔና ተማሪዎች | |

2.8.2.1 የዘመድ/የግል ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግ

የዘመድ ደብዳቤ አፃፃፍ የራሱ የሆነ ፎርም/ ቅርፅ አለው። በዋናነት መግቢያ (ሠላምታ)፣ ሀተታ (ዝርዝር ሀሳብ) እና መደምደሚያ (ስንብት) በማለት የዘመድ ደብዳቤ በሦስት አንቀጽ ተከፍሎ ይፃፋል ማለት ነው። በመሆኑም ሁለት ዙር የተፃፈው የዘመድ ደብዳቤ ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል። የተፃፉ ደብዳቤዎችን ለመገምገም ጥቅም ላይ የዋሉ መስፈርቶችም የሚከተሉት ናቸው።

- የቃላት ፍች/ትርጉም
- ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም
- የአረፍ ተነገር አወቃቀር
- የአረፍተ ነገር መልዕክት
- የአንቀጽ አንድነት
- የአንቀጽ ግጥምጥምነት

ሠንጠረዥ 3፡- የዘመድ ደብዳቤ ጽሑፍ ውጤት

| ተ.ቁ | የጥናቱ ተሳታፊዎች | ፆታ | በመጀመሪያ | | 2ኛ ዙር(ከግብረ መልስ በኂላ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 1 | A | ሴ | 7 | 70% | 10 | 100% | |
| 2 | B | ሴ | 6 | 60% | 8 | 80% | |
| 3 | C | ሴ | 7 | 70% | 9 | 90% | |
| 4 | D | ሴ | 5 | 50% | 9 | 90% | |
| 5 | E | ሴ | 7 | 70% | 10 | 100% | |
| 6 | F | ሴ | 6 | 60% | 10 | 100% | |
| 7 | G | ሴ | 6 | 60% | 9 | 90% | |
| 8 | H | ሴ | 6 | 60% | 9 | 90% | |
| 9 | I | ሴ | 5 | 50% | 10 | 100% | |
| 10 | J | ሴ | 5 | 50% | 8 | 80% | |
| 11 | K | ወ | 5 | 50% | 9 | 90% | |
| 12 | L | ወ | 7 | 70% | 9 | 90% | |
| 13 | M | ወ | 6 | 60% | 10 | 100% | |
| 14 | N | ወ | 7 | 70% | 10 | 100% | |
| | አማካይ | | 6 | 60% | 9.28 | 92.8% | |

ከላይ ሠንጠረዥ 3 ላይ እንደተገለጸው በመጀመሪያ ዙር ላይ ለፈለጉት ዘመድ አዝማድ የዘመድ ደብዳቤን እንዲጽፉ በማድረግ ከአስሩ ታርሞ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክታው ዝቅተኛው 5(50%)፣ ከፍተኛው 7(70%) እና አማካይ 6(60%) ወይም የ4ቱ 5(50%)፣የ5ቱ 6(60%)፣ የ5ቱ 7(70%) ሆኖ ተመዝግቧል። በዚህ ዙር ከጻፉት ደብዳቤ ላይ የታዩ ችግሮች የፊደል ቅርፅ ችግር፣ ትርጉም የማይሰጥ የፊደላት ስብስብ፣ ያለቦታው ስርዓተ ነጥቦችን ማስገባትና አለማስገባት፣ የአረፍተነገር አወቃቀር የቋንቋውን ስርዓት አለመጠበቅ (ባላቤት + ተሳቢ + ማሰሪያ አንቀጽ)፣ አረፍተነገሮቹ ሙሉ መልዕክት አለማስተላለፍ፣ የአንቀጹ ሀሳብ ፍሰቱን ጠብቆ ያለመሄድ ችግር (የአንድነትና ግጥምጥምነት ችግር)፣ ከአንድ በላይ ሀሳቦችን በአንድ አንቀጽ ላይ ቀላቅሎ መፃፍ፣ የዘመድ ደብዳቤ አፃፃፍ ፎርማትን (ቅፅን) አለመከተል፣እና የመሳሰሉት ችግሮች ተስተውለዋል።

2.8.2.2 የመስርያ ቤት ደብዳቤ በቡድን እንዲጽፉ ማድረግ

ሠንጠረዥ 4፡- የመስርያ ቤት ደብዳቤ ጽሑፍ ውጤት

| ተ.ቁ | የጥናቱ ተሳታፊዎች | የአባላት ብዛት | በመጀመሪያ | | 2ኛ ዙር(ከግብረ መልስ በኋላ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 1 | ቡድን 1 | 5 | 8 | 80% | 10 | 100% | |
| 2 | ቡድን 2 | 5 | 7 | 70% | 9 | 90% | |
| 3 | ቡድን 3 | 4 | 8 | 80% | 9 | 90% | |
| | አማካይ | | 7.7 | 77% | 9.3 | 93% | |

ከሠንጠረዥ 4 እንደተገለጸው በመጀመሪያ ዙር የመስርያ ቤት ደብዳቤ በቡድን እንዲፅፉ ተደርጎ ከአስሩ ሲታረም ዝቅተኛው 7(70%)፣ ከፍተኛው 8(80%)፣ አማካይ ድግሞ 7.7(77%) ነው፡፡ ማስተካካያ ግብረ መልስ ከተሰጣቸው በኋላ ሁለተኛ ዙር የመስርያ ቤት ደብዳቤ እንዲጽፉ ተደርጎ አሁንም ከአስሩ ሲታረም የተገኘው ውጤት ዝቅተኛው 9(90%)፣ ከፍተኛው 10(100%) አማካይ 9.3 (93%) በመሆን ተመዝግቧል፡፡ ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው ብዙ ለውጥ መኖሩን ነው፡፡ ከፍተኛ ለውጥ እንዲኖር ያደረገው ደግሞ በቡድን በጋራ ተወያይተው እንዲጽፉ መደረጉ ነው፡፡ ነገር ግን ከፃፉት ላይ የታዩ ስህተቶች የአርፍተ ነገር አወቃቀር ችግር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ችግር፣ የሀሳብ ፍሰት ችግር፣ የአንቀጹ አንድነትና ግጥምጥምነት ችግር እንዲሁም በአንድ አንቀጽ ከአንድ በላይ ሀሳቦችን ማካተት ከታዩት ችግሮች መካከል ናቸው፡፡

2.8.2.3 በመረጡት ርዕስ በጥንድ ሆነው አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ

ሠንጠረዥ 5፡- ራሳቸው ርዕስ መርጠው የፃፉት አንቀጽ ውጤት

| ተ.ቁ | የጥናቱ ተሳታፊዎች | የአባላት ብዛት | በመጀመሪያ | | 2ኛ ዙር(ከግብረ መልስ በኋላ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 1 | ሀ | 2 | 8 | 80% | 9 | 90% | |
| 2 | ለ | 2 | 8 | 80% | 10 | 100% | |
| 3 | ሐ | 2 | 7 | 70% | 8 | 80% | |
| 4 | መ | 2 | 6 | 60% | 8 | 80% | |
| 5 | ሠ | 2 | 6 | 60% | 8 | 80% | |
| 6 | ረ | 2 | 8 | 80% | 9 | 90% | |
| 7 | ሰ | 2 | 7 | 70% | 8 | 80% | |
| | አማካይ | | 7 | 70% | 8.6 | 86% | |

ከሠንጠረዥ 5፡- እንደቀረበው በጥንድ ሆነው(ሀ፣ለ፣…፣ሰ) ራሳቸው በመረጡት ርዕስ አንቀጽ እንዲጽፉ ሲደረጉ ላም፣ ትምህርት፣ እናት፣ አባት፣ ወላጆች፣ ንብ እና ድመት በሚሉት ርዕሶች አንቀጽ ጽፈዋል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ዝቅተኛው 6(60%)፣ ከፍተኛው 8(80%)፣ አማካይ 7(70%) ሲሆን፤ ከግብረ መልስ በኋላ ሁለተኛ ዙር ዝቅተኛው 8(80%)፣ ከፍተኛው 10(100%)፣ አማካይ ደግሞ 8.6(86%) ነው፡፡

ከሠንጠረዥ 4 እና 5 ያለውን ውጤት ስናወዳድረው ሠንጠረዥ 4 ላይ በቡድን ሆነው ሁለተኛ ዙር ላይ የፃፉት አንቀጽ ውጤት አማካይ 9.3(93%) ሲሆን፣ ሠንጠረዥ 5 ላይ በጥድን ራሳቸው በመረጡት ርዕስ ሁለተኛ ዙር ላይ የፃፉት አንቀጽ ውጤት አማካይ 8.6(86%) ነው፡፡ በቡድን የፃፉት አንቀጽ በጥንድ ከፃፉት አንቀጽ የተሻለ መሆኑን ከውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡

2.8.2.4 ርዕስ በመስጠት በግል አንቀጽ እንዲጽፉ ማድረግ

ሠንጠረዥ 6፡- ርዕስ ሲሰጣቸው የፃፉት አንቀጽ ውጤት

| ተ.ቁ | የጥናቱ ተሳታፊዎች | ፆታ | ውጤት | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 1 | A | ሴ | 10 | 100% | |
| 2 | B | ሴ | 9 | 100% | |
| 3 | C | ሴ | 10 | 100% | |
| 4 | D | ሴ | 8 | 80% | |
| 5 | E | ሴ | 9 | 90% | |
| 6 | F | ሴ | 10 | 100% | |
| 7 | G | ሴ | 8 | 80% | |
| 8 | H | ሴ | 9 | 100% | |
| 9 | I | ሴ | 10 | 100% | |
| 10 | J | ሴ | 9 | 100% | |
| 11 | K | ወ | 10 | 100% | |
| 12 | L | ወ | 9 | 90% | |
| 13 | M | ወ | 9 | 90% | |
| 14 | L | ወ | 10 | 100% | |
| | አማካይ | | 9.3 | 93% | |

በግላቸው አንቀጽ እንዲጽፉ በእጣ የተሰጣቸው ርዕሶች በቅሎ፣ እውቀት፣ በሬ፣ ጤና፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ባህል፣ ልብስ፣ ፍቅር፣ ፈረስ፣ ጤፍ፣ ቤት፣ ጓደኝነት እና ምግብ ናቸው፡፡ በእነዚህ ርዕሶች በግላቸው የጻፏቸውን አንቀፆች በማረም ዝቅተኛው 8(80%)፣ ከፍተኛው 10(100%)፣ አማካይ ደግሞ 9.3(93%) ሆኗል፡፡ በዚህ በግላቸው ከፃፉት አንቀጽ ላይ የታዩ ችግሮች የአንድነት፣ የግጥምጥምነት፣ በአንድ አንቀጽ ላይ ከአንድ በላይ ሀሳቦችን ማካተት እንዲሁም ነጠላ ሰረዝ እና ድርብ ሰረዝ ስርዓተ ነጥቦችን ያለቦታቸው መጠቀም በተለይ ሁለቱ ሴቶች ላይ ጎልተው የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን ውጤታቸው ማሳያ ነው፡፡

**2.9 ጽብረቃ**

በአጠቃላይ በ2014 ዓ.ም የማታ መማሪያ ክፍል ‹‹02›› አስር ሴቶችንና አራት ወንዶች ሰልጣኞችን አንቀጽን መጻፍ ችግራቸውን ለመቅረፍ የተደረገው ድርጊታዊ ምርምር ችግሩ ከተለየበት ጥቅምት ወር ጀምሮ ችግሩን ለመፍታት ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ተግባራት እስከተከናወኑበት ድረስ በርካታ ጊዜያትን ወስዷል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ሰልጣኞችን ተከታታይ ሶስቱንም አመት ስለማስተምራቸው በቅርበት የመከታተልና የመለየት እድል ነበረኝ፡፡ በመሆኑም በ2014 ዓ.ም አንደኛ ሰሚስተር **የዘገባ አፃፃፍ (MT 321)** የሚል ኮረስ ለማስተማር በዚህ ክፍል ተመደብኩኝ፡፡ በመሆኑም ያለፉትን ሁለት

አመታት የተለያዩ ኮርሶችን በማስተምርበት ጊዜ የተለያዩ ተግባራትን እንዲጽ ሲታዘዙ ጎልቶ የሚታየው ችግር ሀሳባቸውን በትክክል በአንቀጽ አደራጅተው ማስተላለፍ አይችሉም፡፡ ይህንን ችግር በመደበኛው ክፍለ ጊዜ ለመፍታት ብሞክርም ሊሳካልኝ አልቻለም፡፡ በተለይም የአንቀጽ መጻፍ ችግር ጎልቶ የሚታየው ከ14 ሰልጣኞች ነው፡፡ ችግሩን ሶስቱንም አመት ስመለከተው የነበርኩት ስለሆነ መፍታት እንዳለብኝ ወሰንኩኝ፡፡ ከዚያም የችግሩን መንስኤ በመለየት ችግሩን ሊፈቱ የሚችሉትን የተለያዩ ተግባራት በማቀድና በእቅዱም መሰረት በመተግበር ውጤቶችን ማየት ተችሏል፡፡ ከሠንጠረዥ 3 እስከ 6 ያሉትን የጽህፈት ተግባራት ውጤቶችን ስንመለከት ለእያንዳንዱ ተግባራቸው ግብረ መልስ እየተሰጣቸው እንዲጽፉ ሲደረግ ከፍተኛ በሚባል ደረጃ አንቀጽን መጻፍ ተሻሽሏል፡፡ ከሁለት ሴቶች በስተቀር የተገኘው ውጤት ከፍተኛ ለውጥ የታየበት ነው፡፡

ስለዚህ የሰልጣኞች አንቀጽን መጻፍ ችግራቸው መቶ በመቶ ባይባልም ተቀርፏል ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ የፊደላትን ቅርፅ በትክክል መፃፍ ችለዋል፤ ትርጉም ያለውን ቃል በጽሑፍ ውስጥ መጠቀም ችለዋል፤ ሥርዓተ ነጥቦችን ነጠላ ሰረዝንና ድርብ ሰረዝን አገባብ ባይለዩም በከፊልም ቢሆን መጠቀም ችለዋል፤ የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቀው (ባለቤት-ተሳቢ-ማሰሪያ አንቀጽ) አረፍተ ነገር መመስረት ችለዋል፤ ህዳግ ጠብቀው መፃፍ ይችላሉ፤ የአንቀጹን ሀሳብ ፍሰት ጠብቀው መጻፍ ችለዋል፡፡ የአንቀጽን ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ባህርያት እና አፃፃፍ ስልቱን በሚገባ ተረድተው ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን በአንቀጽ ጽፈው ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ የነበራቸውን አመለካከት በመቀየር አንቀጽን ለመፃፍ ተነሳስተዋል፤ ፍላጎትም አሳድረዋል፡፡ በጠቅላላው ሰፊ ለውጥ ታይቷል፡፡

### 2.9.1 የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች

- ለመቅረፍ አልሞ የተነሳውን ችግር መቅረፍ መቻል፤
- ከመደበኛው መማር ማስተማር በተጨማሪ በድርጊታዊ ምርምር ችግሩን መፍታት መቻል፤
- ተጠኚዎቹ አብዛኞቹ በትርፍ ሰዓት ስራ እየሰሩ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተምሩ በመሆናቸው አመቻችተው በተቃራኒ ፈረቃቸው ፈቃደኛ ሆነው በመምጣት ጥናቱ ግብ ላይ እንዲደርስ ማድረጋቸው፤
- የጊዜ ችግርንና የስራ መደራረብን ተቋቁሞ መስራት መቻል፤
- አንቀጽን ለመጻፍ ትኩረት ሰጥተው መለማመድ መቻላቸው፤
- የተሰጣቸውን ተግባር ሁሉ በፈቃደኝነት መስራታቸው ወ.ዘ.ተ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

### 2.9.2 የጥናቱ ደካማ ጎኖች

- ተጠኚዎቹ ቲቶሪያል ሲጠሩ ሰዓት አለማክበር፣ ማርፈድ እንዲሁም መቅረት፤
- መማር ማስተማር ጋር ጎን ለጎን የሚካሄድ በመሆኑ የጊዜ ማጠር ችግር፤
- ተጠኚዎቹ ግብረ መልስን ቶሎ ያለመቀበል ችግር ከደካማ ጎኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 2.10 ከዚህ ድርጊታዊ ምርምር ምን ተማርኩ

- በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በድርጊታሚ ምርምር መቅረፍ እንደሚቻል፤
- ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን ጊዜውን አብቃቅቶ ምርምር ማድረግ እንደሚቻል፤
- ችግሩን ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ ሰፊ ጊዜና ልዩ ልዩ ተግባራት እንደሚያስፈልጉ፤
- የተለያዩ ተግባራትን በመስጠት ሳይውል ሳያድር ግብረ መልስ ቶሎ መስጠት በፍጥነት የሚፈለገውን ለውጥ ማስገኘት እንደሚቻል፤
- ጽፍፈትን ስናስተምር በገለፃ ከማስተማር ይልቅ በተግባር ማለማመድ እንደሚገባን፤
- ድርጊታዊ ምርምር ለማድረግ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ሰው፣ እና እውቀት አስፈላጊ መሆኑን ተምሬበታለሁ፡፡

## 2.11 አስተያየት

- ሁሉም የሚመለከታቸው የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም የትምህርት አመራሮችና መምህራን ዕለት ተዕለት በመማር ማስተማር ተግባር ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየትና በማቀድ ድርጊታዊ ጥናትና ምርምር በማድረግ በከፊልም ቢሆን ችግሮችን መቅረፍ ስለሚቻል መስራት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡
- አንቀጽ መጻፍን የተለያዩ ተግባራትን በማዘጋጀትና ግብረ መልስ በመስጠት በተግባር ማለማመድ ቢቻል የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡
- ለጽህፍት መሰረቱ ፊደል በመሆኑ የፊደል ቅርፆችን ትኩረት ሰጥቶ ለመለየት የፊደል ገበታው መለየት የለበትም፡፡
- ተማሪዎችን ከግል ተግባራቸው በተጨማሪ በቡድንና በጥንድ በጋራ ተወያይተው የሚጽፉትን የጋራ ተግባር ብንሰጥ የበለጠ መማማር ይችላሉ፡፡
- አንቀጽን መጻፍ የተግባር ልምምድን የሚፈልግ መልዕክት/ሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን ከምርምሩ መረዳት ተችሏል፡፡
- የጥናቱ ተተኳሪዎች 98% ያክሉን ችግር ቀርፈዋል፤ ቢባልም 2% ያክሉ ችግር ያልተቀረፈ መሆኑን ከላይ ከሰንጠረዦች ከተገለፀው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.12 ለቀጣይ የስራ አቅጣጫ

ድርጊታዊ ምርምር ቀጣይነት ስለሚኖረው እና ችግሩ ሙሉ በሙሉ ስለማይቀረፍ ቀጣይ በአዲሱ በማቀድ እና የተለያዩ ተግባራትን በማዘጋጀት ችግሩን የበለጠ እየፈቱ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጠንካራ ጎኑን በመውሰድ እንዲሁም ከደካማ ጎኑ ደግሞ በመማር ሰፊ ጊዜ በመውሰድ በተሻለ ሁኔታ መስራት ይጠበቃል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው የተሻሻለ ሁለተኛ እትም* ፡፡አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ት/ሚ፡፡ (2004)፡፡ *የዘጠነኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ* ፡፡ አዲስ አበባ፣ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

Harmer ,J. (1991). *The practice of English Language teaching*. Harlaw, UK;Longman.

Jordan ,R.R.(1980). *Academic writing course*. London; Butter and Tammer Ltd.

Lewis, M and Hill,J. (1985). *Practical techniques for language teaching*. London; commercial colour press.

Stern ,H.H. (1983). *Fundamental concept of language learning and teaching*. Oxford; oxford university press.